# የመምሪያው ዓመታዊ ሪፖርት

## <u>መግቢያ</u>

የአቅም ግንባታ መምሪያ ከተቋቋመበት አላማ አንፃር የተሠማራበትን አላማ ለማስፈፀም መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በማድረግ በዋናና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በመደራጀት በዞኑ በሚገኙ 15 ወረዳዎችና በ2ቱ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ተቋማትና የሲቪል ሠርቪሱን የማስፈፀም አቅም መገንባትና የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ስርጸ የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ ለመምጣት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አከናውኗል።

በዚሁ መሠረትም የማስፈፀም አቅም ግንባታ በአሠራር በአደረጃጀትና በስልጠና የሰው ኃይል ልማት ቅንጅታዊ ተግባራት ሀገሪቱና ክልሉ የሚከተሉትን የልማት እንቅስቃሴ በማገዝ ጉላ ያለ ድርሻ አለው። ከዚህ በመነሳት የአቅም ግንባታ ተግባራት ከዞን እስከ ወረዳ በተለያዩ ሁኔታ ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

በመሆኑም መምሪያው በ2001 ዓ.ም. ከዞን እስከ ወረዳ ያከናወናቸውን ተግባራት እና ያስመዘገባቸውን ውጤቶች እንደሚከተለው ተገልጿል።

❖ *የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ባጠናቀቁ 7 ሴክተሮች ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ማሸጋገርና ወደ ለውጡን መሬት ማስረገጥ ይቻል ዘንድ የተደረገ አፈፃፀም በሚመለከት ፣*

በለውጥ ኘሮፖራሞችና ፖኬጆች ጥናትና ትግበራ የሥራ ሂደት በኩል በዚህ ዓመት የተከናወኑ ተግባራት በሁለት ክፍሎች ይከፈላሉ :-

1. *የሙከራ ትግበራ ዕቅድና ክንውን አፈፃፀም*
2. *መደበኛው ዓመታዊ ዕቅድና ክንውን አፈፃፀም*

የሙከራ ትግበራ እቅድ ክንውን በተመለከተ ሙከራው የተተገበረው በዞን ማዕከል ፣ በዳምባ ጎፋ ወረዳ እና በአርባ ምንጭ ከተማ አስተዳደር ሲሆን ለሙከራ የተመረጡት ተቋማት በዞን ደረጃ የአርባ ምንጭ ሆስፒታል እና የአርባ ምንጭ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በዳምባ ጐፋ ወረዳ አ/ቅ/ግ/ጽ/ቤት የሣውላ ከተማ ጤና ጣቢያ እና በአርባ ምንጭ ከተማ አስ/አቅም ግንባታ የአርባ ምንጭ ከተማ ጤና ጣቢያ ሲሆኑ ለሙከራ የተመረጠው ኘ ሮጀክት የቅሬታ ማስተገኛ ሥርዓት ዝርጋታ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጥ ያልረካ ተገልጋይ ቅሬታውን ያለምንም መሸማቀቅ አሰምቶ ምላሽ የሚያገኝበት ሥርዓት መፍጠር ነው:: ይህንንም እውን ለማድረግ ፣

## ሀ. <u>አቅም የመገንባት ሥራ</u>፣

በሁለቱም ተቋማት/ በአርባ ምንጭ ሆስፒታል እና በአርባ ምንጭ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት / ለ33 ሠራተኞች ስለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ፣ ስለመልካም አስተዳደር ፣ ስለአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም ፣ እና ስለተገልጋዮች ቅሬታ አቀባበል ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል ::

## ለ. <u>የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓቱን በመዘረጋት ረገድ</u> ፣

በሁለቱም ተቋማት/ በአርባ ምንጭ ሆስፒታል እና በአርባ ምንጭ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት / በሠራተኞች የነቃ ተሣትፎ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት አካላት እንዲመረጡ የተደረገ ከመሆኑም በላይ ለእነዚህ አስፈፃሚ አካላት እስከ ሥራ ክፍል ድረስ ያሉትን አባላት ያሣተፈ የሥራ ማስጀመሪያ ሥልጠና ተሰጥቶ ያለባቸው ክፍተት እንዲለዩ ከተደረገ በኂላ የመነሻ እቅድ በማዘጋጀት በመ/ቤታቸው ተጨባጭ ሁኔታ አስማምተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጐ ተገልጋዩ በአገልግሎት አሰጣጡ የተሰማውን ቅሬታ ያለመሸማቀቅ የሚገልጽበት ሥርዓት በተቋማቱ ተተክሏል::

ሌላው የሙከራ ትግበራ እቅድ የነበረው የተቀናጀ እቅድ ዝግጅትና የትግበራ አፈፃፀም ክፍተት ጥናት ሲሆን ከክልሉ የሚወርዱ እቅዶች የተቀናጁና ውጤታማ እንዲሆኑ ከወረዳዎች ተጨባጭ

ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ችግሮች የሚለዩበት ግብአት ከተመረጡ ሶስት የወረዳ ቀበሌያት ተሰብስቦ ፣ ተተንትኖና ተጠናቅሮ ለክልሉ አቅ/ግ/ቢሮ ተላልፎ የዞናችንን ትክክለኛ ገጽታ ጠቋሚ ሰነድ በክልሉ አግ/ቢሮ እጅ እንዲኖር ተደርጓል፡፡

በዚህ የሙከራ ትግበራ ወቅት የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን በሁሉም ሠራተኛው ውስጥ ለማስረጽ የ20 ዞን እና ዞናዊ ባህርይ ላላቸው ጽ/ቤቶች እና የ15ቱ ወረዳና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር አ/ግ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉበት ፎረም ተዘጋጅቶ የለውጥ አቅጣጫ ላይ የጠራ አቋም ለማስያዝ መሠረት ተጥሏል፡፡ ድጋፍና ክትትልንም በሚመለከት በሙከራ ተግባሪ ጽ/ቤቶች በሣምንት ለ2 ሰዓት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በዚህም የሙከራ አፈፃፀሙ በክልሉ ሙከራ ካደረጉት የተሻለ ውጤት የታየበት እንደሆነ በተደረገው የጋራ መድረክ ቀርቧል፡፡

ከዚህ ውጪ ለሙከራ የተመረጠው የደንባ ጉፋ አ/ግ/ጽ/ቤት በማውላ ጤና ጣቢያ ፣ የአርባ ምንጭ ከተማ አ/ግ/ጽ/ቤት በአርባ ምንጭ ጤና ጣቢያ እያደረገ ያለውን ሙከራ ውጤታማ እንዲሆን ሁለት ዙር በመደገፍ ተቋማቱ ያለባቸውን ክፍተቶች መሠረት ያደረገ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቶ በየተቋማቱ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶ እንደሥርአት ተተክሎ የተገልጋይ የእርካታ አስተያየት ለማግኘት ተችሏል፡፡ ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው 10 መ/ቤቶችም በሪፎርም አፈፃፀም ዙሪያ ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ሙከራውን በአጠጋቢ ሁኔታ ወደ ሙሉ ትግበራ ለማሸጋገር ታቅዶ ይኸው 100 % ተከኗውኗል፡፡

## 2. መደበኛው ዓመታዊ እቅድ ክንውን አፈፃፀም

በክልላችን የተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ጥናት ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ሽግግር ሲደረግ በድልድል ደንቡ እና በማስፈፀሚያ እስሪቴጂው ላይ ከ20 ዞንና ዞናዊ ባህርይ ላላቸው መምሪያዎች ፣ ለ15ወረዳ ጽ/ቤቶች እና በ2ቱ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ፈፃሚዎች ለአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቶ ግንዛቤ በማስጨበጥ ወደ ድልድሉ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ፈፃሚው በድልድል ደንቡ ፣ በጥናት ሰነዱ በሚጋብዘው የሙያ መስመር ፣ በትምህርት ዝግጅት እንዲሁም አግባብ ባለው የሥራ ልምድ አሟልተው ስለመደልደላቸው በየሴክተሮች ተገኝቶ በማጣራት የተጠናቀረ መረጃ ለክልሉ አ/ግ/ቢሮ እና ለዞኑ ስትሪንግ ኮሚቴ የተላለፈ ሲሆን በአፈፃፀም በታዩ ክፍተቶችም ድጋፍ ተሰጥቷል ፡፡ በተጨማሪም ከድልድል የተረፉ ሠራተኞችን መረጃ እና በድልድል ያልተያዘ ክፍት መደቦችን በማጠናቀር ለግብረ ኃይሉ ተላልፎ የተንሣፈፈው ሠራተኛ ድልድል እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ አጠቃላይ መረጃውን ስንመለከት ድልድል ያገኘ ---------- ከተደለደለው ስልጠና የወሰደ --------- ያልወሰደ ---------- ከድልድሉ የተረፈ --------- በሰው ኃይል ያልተያዘ -------------- መሆኑን ያመላክታል፡፡

በተመረጡ በዞን 7 ሴክተሮች ፣ በ15 ወረዳ እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ሠራተኛው በጥናት ሰነዱ በተቀመጠው እስታንዳርድ መሠረት እቅዱን በመፈፀም ጥናቱን መሬት በማስረገጥ ለውጡን በተቋማት እንደስርአት መትከል ይቻል ዘንድ በየተቋማቱ በ15 ቀን ለአንድ ቀን ከ2:00 ሰዓት በላይ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል፡፡

በሌላ መልኩ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን ተቋማዊ መልክ ለማስያዝ በወረዳ ለሚገኙ ጽ/ቤቶች በተቀመጡ በጥረት ተደራሽ ግቦች ፣ ከሚጠበቁ ውጤቶች እና እስታንዳርድ መሠረት እንዲፈፀም ድጋፌዊ ከትትል ተደርጐ በአፈፃፀም መሻሻል ታይቷል ። ከዚህ ባሻገር የአመለካከት እና የአፈፃፀም ለውጥ ለማምጣት የሠራተኛውን ግንዛቤ በማሣደግ የለውጥ ኃይሎችን ለማበራከት ለ500 ሰራተኞች አጫጭር ስልጠና በመስጠት የፈፃሚውን አቅም ለማብቃት ተችሏል ።

ከዚህም ባሻገር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን እንደ ሥርዓት አድርጎ በየተቋማቱ ለመትከል የየተቋቱን የሂደት አስተባባሪዎች በአቅም ግንባታ ሰብሣቢነት በወር አንድ ቀን በማገናኘት ፣

- በየሥራ ሂደቱ ለውጡ ያለበትን ደረጃ በመገምገም
- በአፈፃፀም ባጋጠሙ ችግሮች ዙሪያ
- የተገልጋዮች የእርካታ መጠን ግምገማ ዙሪያ
- የተሞክሮ ልውውጥ በማድረግ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ተቋማዊ መሠረት እንዲይዝ መሠረት ተጥሏል።

በተጨማሪ ወደ ትግበራ በገቡ ሴክተሮች የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የዳሰሳ ጥናት ተደርጐ የጥናቱ አፈፃፀም ያለበት ደረጃ ፣ በአፈፃፀም የታዩ ክፍተቶች ፣ በአፋጣኝ ውሣኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ተለይተው እና ተጠናቅረው ለሚመለከተው ክፍል ተላልፎ በየታየው ክፍተት ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

በመሆኑም በዞን ጥናቱ የተጠናቀቀባቸው ሴክተሮች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ዙሪያ ያላቸው አፈፃፀም ስንመለከት ፣

- አቅም ግንባታ ፣ ንግድ ኢንዱስትሪ ፣ አርባ ምንጭ ማረሚያ ፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሻለ አፈፃፀም ያሳዩ ሲሆን ፣
- ፖሊስ ፣ ፍትህና ፀጥታ ፣ ሥራና ከተማ ልማት ፣ ትምህርት መካከለኛ አፈፃፀም ያሳዩ ሲሆን ፣
- ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ በአፈፃፀም ክፍተት ታይቶበታል።

***የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት*** በሁሉም ወረዳዎች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ተቋማዊ መሠረት እንዲኖረው በ15 ወረዳ እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች የመነሻ እቅዶችን ፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ እና ማጠናቀሪያ ፎርማትን ፣ እንዲሁም የአፈፃፀም ማኑዋሎችን በማሠራጨት እና ተደጋጋሚ ድጋፍ እና ክትትል የተደረገ ሲሆን በዚህም ፣

➢ ቁጫ ፣ ዳራማሎ ፣ ዳምባ ጕፋ ፣ ዑባ ደብረ ፀሐይ ፣ ሣውላ ከተማ አስተዳደር እና ዲታ የተሻለ አፈፃፀም ያሣዩ ሲሆን ፣

➢ ካምባ ፣ ቦረዳ ፣ ዛላ ፣ አ/ም/ከተማ/አስዳደር ፣ መካከለኛ አፈፃፀም ሲኖራቸው ፣

➢ አ/ም/ዙሪያ ወረዳ ፣ ም/አባያ ፣ ጨንቻ ፣ ጌዜ ጕፋ እና ኦይዳ ፣ መሎ ወረዳ በአፈፃፀም ክፍተት የታየባቸው በመሆኑ በአፈፃፀማቸው የተለየ ድጋፍ እየተደረገላቸው ከመሆኑም በላይ በወረዳ ደረጃ የለውጥ ኃይሎችን ለማበራከት እና የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን በሁሉም የህብረተሰብ አካላት ለማስረጽ በዚህ ሩብ ዓመት ሁለት ብሮሸሮች ተዘጋጅተው የተሠራጨ ሲሆን አዳዲስ ወደሥራ ለሚገቡ ፈፃሚዎችም አጭጭር ስልጠናዎችን በመስጠት የማብቃት ሥራ የተሠራ በመሆኑ በዓመቱ 100% ለውጡን መሠረት ለማስያዝ አቅደን 100% ተሸፍኗል።

❖ **የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ የእንስፔክሽን አደጃጀትን ተግባራዊ በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትንና የተመዘገቡ ውጤቶችን በሚመለከት ፣**

የመልካም አስተዳደር ፖኬጁን ተግባራዊ ለማድረግ ፈጻሚዎች በእውቀት ሥራውን ማከናወን እንዲችሉ የእቅድ እንስፔክሽን እና ሱፐርቪዥን አደረጃጀት እና አሠራር ማስፈጸሚያ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በማሠራጨት ፣ በአፈፃፀሙ ግንዛቤ በመፍጠር ፣ ድጋፍ እና ክትትል በተደረገው መሠረት

በቁጫ ፣ ኡባ -ደብረ ፀሐይ ፣ ጌዜ ጕፋ ፣ ዳንባ ጕፋ ፣ ዳራማሎ ፣ ዛላ ፣ ካምባ ፣ ዲታ ፣ ቦረዳ ፣ ቦንኬ ወረዳዎች የእንስፔክሽን እና ሱፐርቩዥን አካላት በሁሉም ቀበሌያት የተቋቋሙ ሲሆን በኦይዳ ፣ ጨንቻ ፣ ምዕራብ አባያ ፣ መሎ ወረዳዎች አካላቱ ያልተደራጁና ወደ ሥራ ያልገቡ በመሆኑ ተደራጅው ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ተደርጐ ወደ ሥራ ገብተዋል ፡ በሌላ መልኩ በ15ቱም ወረዳ ቀበሌያት ፣ የቀበሌያት ሥራ አስኪያጆች ተቀጥረው የተቀናጀ እቅድ በማዘጋጀት የመረጃ ተቀባይ ሥርዓት በመዘርጋት የተቀላጠፈ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በተጨማሪመ በየወረዳው የሚገኙ ቀበሌያትን በክላስተር በማደራጀት ለድጋፍና ክትተል ፣ ለእቅድ አፈፃፀም ለተሞክሮ ልውውጥ እና ለበርካታ ሥራዎች ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ በመሆኑ የዓመቱን ክንውናችንን ስንመለከት በዚህ ዓመት የእንስፔክሽን አደረጃጀትን 100% ለመፈፀም ታቅዶ ይህው ተግባራዊ ስለሆነ የዓመቱ ክንውናቸችን 100% ተከናውኗል ።

❖ **ህብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሳተፍና አሳምኖ የማሰራት ባህልን በማዳበር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራርን በመዘርጋት በህዝቡ ተሰትፎ እቅድ የማዘጋጀት እና ሞዴል አመራረጥ እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋፋት አፈፃፀምን በሚመለከት ፣**

የተቋሙን እቅድ ስኬታማና ውጤታማ ለማድረግ ከ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት እና ከ2ቱ ከተማ አስተዳደር ለተውጣጡ አመራሮች እና ባለሙያዎች በእቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም ፎረም ተዘጋጅቶ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ ህብረተሰቡ ያመነበትን ሥራ በራሱ ተነሳሽነት የተለያዩ የልማት እቅዶችን አቀናጅቶ ወደ ሥራ እንዲገባ የእቅድ አዘገጃጀት ንድፈ ሀሣብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ማኑዋል እንዲሁም የሞዴል መንደርና አርሶ አደር መምረጫ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በማሠራጨት የማስፈፀሚያ አቅምን የማጉልበት ሥራዎች በመስራት እና በአካል በወረዳዎች በመገኘት ድጋፍ የተደረገና አፈጻጸሙ የዕቅዱ 100% ሲሆን የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት ፣

ዲታ ፣ ኡባ -ደብረ ፀሐይ ፣ ጌዜ ጎፋ ፣ አይዳ ፣ ደንባ ጎፋ ፣ ዳራማሎ ፣ ቁጫ ፣ ዛላ ፣ ካምባ ፣ ቦረዳ ወረዳዎች በህብረተሰቡ ተሣትፎ በሁሉም ቀበሌያት የተቀናጀ እቅድ አዘጋጅተው ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን ጨንቻ ፣ አርባ ምንጭ ዙ/ወረዳ እና ምዕራብ አባያ ፣ መሎ ወረዳዎች የመነሻ እቅድ ከማዘጋጀት እስከ አፈፃፀም ማኑዋሎች በማሠራጨት ድጋፍና የተደገላቸው ቢሆንም በቀበሌያት ሥርዓቱን ለመዘርጋት የተጠናከረ አፈፃፀም ያላሣዩ በመሆኑ በአጭር ጊዜያት ወርደው ሥርዓቱን እንዲዘረጉ ድጋፍና ክትትል በተደገላቸው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋፋት ልማቱን ለማፋጠን የሞዴል መምረጫ መመሪያዎችን በማሠራጨት ወረዳዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ በተሰጠው ድጋፍ በሁሉም ወረዳዎች ሞዴል ቀበሌያት እና ሞዴል አርሶ አደሮች ተመርጠው መረጃዎች የተጠናቀሩ እና ለቴክኒክ ኮሚቴው የተላለፈ ሲሆን የሁሉም ቀበሌያት ፣ የወረዳ ጽ/ቤቶችና የዞን መምሪያዎች የአፈፃፀም ደረጃ ወጥቷል፡፡ የሞዴል አርሶ አደር ተከታዮች መረጃ ከቁጫ እና ዲታ ወረዳዎች በስተቀር በሌሎች ተለይቶ ያልተጠናከረ በመሆኑ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋፋት የሞዴል አርሶ አደር ተከታዮችን ቁጥር በማበራከት ወደአለምነው ግብ ለመድረስ አጋዥ ኃይል ስለሆነ ተጠናክሮ እንዲሠራ በተሰጠው ድጋፍ ወደ ሥራ እየገቡ ይገኛሉ ፡፡ በሁሉም ቀበሌያት የሚገኙ ሥራ አስኪያጆች በእቅድ ዝግጅት እና ሪፖርቲንግ ዙሪያ ስልጠና አግኝተው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዓመት 100% ሥርዓቱን ለመዘርጋት ታቅዶ 100% ተከውኗል ፡፡

- የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት የፍትህ አካላቱን የማስፈፀም አቅም በማጉልበት እና የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ አስፈፃሚ አካላት

**በመሰየም እቅድ በማዘጋጀትና እቅዱን ተፈፃሚ በማድረግ ቅድመ ወንጀል መከላከልና እና ወንጀል በመነቀስ ተደራሽ ውጤት ከማስመዝገብ አኳያ ያለውን አፈፃፀም ስንመለከት ፣**

የፍትህ አካላቱን / ፍርድ ቤት ፣ ፖሊስ ፣ አቃቤ ህግ እና ማረሚያ ቤቶች/ የማስፈፀም አቅም ለማጐልበት ፣ ከ15ቱ ወረዳ እና ከ2ቱ ከ/አስተዳደር በተውጣጡ ፍትህ አካላት መካከል ፎረም በማዘጋጀት በፍትህ ሥርዓት አገልግሎት አሰጣጡ ውይይት በማካሄድ እና የልምድ ልውውጥ በማካሄድ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል ። በሌላ መልኩ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ በየፍትህ ሴክተሩ በ15 ቀን አንድ ጊዜ በመገኘት ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር በወር አንድ ቀን የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲጐለብት የተደረገ ሲሆን በህብረተሰቡ ተሣትፎ ወንጀልን ከሥሩ ለማድረቅ የተቀናጀ እቅድ በመዘርጋት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ማስፈፅሚያ መመሪያ ለዞን ፍትህ ሴክተሮች ፣ ለ15ቱ ወረዳ እና ለ2ቱ ከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ እና ፍትህ ሴክተሮች ከመሠራጨቱም በላይ የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ ፣ የፍትህ አካላት ፣ የሐይማኖት ተቋማት ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ ክፍለ - ከተማዎች ፣ ቀበሌያት እና ታዋቂ ግለሰቦችን ያሣተፈ ውይይት በማካሄድ ከዞን እስከ ቀበሌ የሚያገለግል እቅድ ተዘጋጅቷል።

***በዚህ ዙሪያ የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት*** *የማስፈፀሚያ ማኑዋል ለወረዳዎች የተሠራጨ እና በድጋፋዊ ክትትል ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የተሠራ ሲሆን ደንባ ጐፋ ፣ ቁጫ ፣ ዳራማሎ ፣ ሣውላ ከተማ አስተዳደር በሁሉም ቀበሌያት የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ አካላት የሰየሙ ሲሆን የተቀናጀ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባትን በሚመለከት ዳራማሎ እና ሣውላ ከተማ አስተዳደር በሁሉም ቀበሌያት ያዘጋጁ ሲሆን ኡባ ደብረ ፀሐይ በ8 ቀበሌያት ፣ ዲታ በ14 ቀበሌያት አይዳ በ2 ቀበሌያት እቅድ አዘጋጅተው ወደ ሥራ ገብተዋል። በተቀሩት ወረዳዎች አካላቱን ከመሰየም ያለፈ ተግባር ያላከናወኑ በመሆኑ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ አፈፃፀም መመሪያዎችን እና ብሮሸሮችን በድጋሚ ለወረዳዎች በማሠራጨት ወደ ሥራ ገብተዋል።*

*በአጠቃላይ የፍትህ አካላት ለህብረተሰቡ እየሰጡ ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የዳሰሳ ጥናት ተኮሄዶ የተጠናቀቀ ሰነድ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፎ የታየውን ክፍተት በመለየት ድጋፍም ተሰጥቷል። በመሆኑም በዚህ ዓመት 100% ለመፈፀም አቅደን ይህንኑ ተፈፃሚ ያደረግን በመሆኑ የዚህ ዓመት ክውን 100% ተፈጽሟል።*

- ***የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲን በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በማሳለጥ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት ፣***

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቆ ወደ ትግባራ ያልገቡ እና ጥናታቸው ተጠናቅቆ ወደ ትግበራ የገቡ ሴክተሮችን በሁለት በመክፈል የአፈፃፀም እቅድ እና አጀንዳዎችን እንዳሉበት ሁኔታ ለይቶ በማዘጋጀት በየሴክተሩ በ15 ቀን አንድ ጊዜ ለሁለት ሰዓት ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው በአገልግሎት አሰጣጡና በሪፎርም አፈፃፀም እንዲሁም ጥናት በተጠናቀቀበቸው በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት አፈፃፀም ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን በወር አንድ ቀን በአቅም ግንባታ የለ/ኘ/የኘ/ጥ/ት/የሥራ ሂደት ሰብሣቢነት ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው የየሴክተሩ የሪፎርም አካላት ጥናቱ በተጠናቀቀባቸው የሂደት አስባባሪዎች የጋራ መድረክ በመፍጠር በየተቋሙ ያልተፈቱ ለአገልግሎት አሰጣጡ አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮች ወደ ጋራ መድረኩ እየቀረቡ የሚፈቱ ሲሆን የልምድ ልውውጥም በተደረገው የአመለካከት ለውጥ መጥቷል ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ቀደም ሲል ከነበረበት መሻሻል አሳይቷል::

በሌላ በኩል ወደ ትግበራ ባልገቡ ሴክተሮች የአገልግሎት አሰጣጡ እና የሪፎርም አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ ለመለየት የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ለሚመለከተው ክፍል የተላለፈ ሲሆን በታየው ክፍተትም ድጋፍ ተሰጥቷል::

***በተመሳሳይ መልኩ በወረዳዎች ያለውን አፈፃፀም*** ስንመለከት የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ የአስፈፃሚውን አካል አቅም ለማጐልበት በዚህ ዓመት 4 ጊዜ ወደ ወረዳዎች ተወርዶ ድጋፍ የተሰጠ ሲሆን በቁጫ፣ ዳራማሎ ፣ ደንባ ጐፋ ፣ ኡባ-ደብረ ፀሐይ ፣ ሣውላ ከተማ አስተዳደር ፣ ዲታ ፣ ካምባ እና ቦረዳ ወረዳዎች በአገልግሎት አሰጣጡ የተሻለ አፈፃፀም የታየ ሲሆን በተቀሩት ኦይዳ ፣ ጌዜ ጐፋ ፣ አ/ምንጭ ዙሪያ ፣ ጨንቻ ፣ ምዕራብ አባያ ፣ ዛላ ፣ ቦንኬ ፣ መሎ ወረዳዎች ፣ የአርባ ምንጭ እና ሣውላ ከተማ አስተዳደር በአፈፃፀም ክፍተት የታየባቸው በመሆኑ ለአፈፃፀም የሚረዳቸው የመነሻ እቅድ ፣ ለሥራው የሚያጋዙ ቅጻ-ቅጾች እና የማስፈፀሚያ ኘሮግራሞች በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ በተሰጠው ድጋፍ ወደ ሥራ ገብተዋል ። በመሆኑም ዓመት 100% ለመፈፀም ታቅዶ ይህው የተከናወነ በመሆኑ የዓመቱ ክንውን 100% ተሸፍኗል::

- ***የአገሪቱን ራዕይ ከማሣካት አኳያ እቅዶችን በማስተሳሰር በተቋማት እንደ ሥርአት ለመትከል የጽ/ቤቶችን እስትራቴጂክ ፣ ዓመታዊ እና ውጤት ተኮር እቅድ አቀናጅቶ በመዘርጋት በመንግሥት ተቋማት እንደ ሥርአት መትከልን በሚመለከት ፣***

የየተቋማቱ እቅድ ከአገራዊ ራዕይ የተመነዘረ ስትራቴጅክ እቅድ በመንድፍ ከዚሁ የተወሰደ ተቋማዊ ፣ የሥራ ክፍል እና የሠራተኛ ውጤት ተኮር እቅድ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ

እና ክትትል በማድረግ እቅዱን በዚሁ መሠረት እንዲከልሱ ከመደረጉም በላይ የሠራተኛው ውጤት ተኮር እቅድ ምዘና በሜሪቱ መሠረት መከናወኑን በማጣራት በታዩ ክፍተቶች ድጋፍ ተሰጥቶ የተሻለ እቅድ ዝግጅትና ምዘና ተደርጓል ፡፡

በሌላ በኩል ሴክተሮች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በሙከራ ተግበር ፣ ከሙከራ ተግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ የሽግግር ወቅት በሥልጠና እና በተያዩ ምክንያቶች የባከኑ ጊዜያቶች በመኖራቸው የአመቱን እቅድ ለማሣካት ከጊዜው አኳያ እየቃኙ እቅዶችን እንዲከልሱ በተሰጠው ድጋፍ የተሻለ አፈፃፀም ታየቷል፡፡

የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት በሁሉም ወረዳ ጽ/ቤቶች ስትራቴጅክ እቅድ የተዘጋጀና ከዚያ ላይ የተመነዘረ የሴክተሩ አመታዊ እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን ሠራተኛው የውጤት ተኮር እቅድ ዝግጅት ምዘናን በሚመለከት የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቆ ከሙከራ ወደ ሙሉ ተግበራ የገቡ መ/ቤቶች የሚመዘኑ በሚዛናዊ ውጤት ተኮር እቅድ ሥርዓት /ቢ.ኤስ.ሲ/ ሲሆን ጥናቱ ተጠናጠናቅቆ እስኪወርድ በጥናት ሰነዱ በተቀመጠው እስታንዳርድ መሠረት እየፈፀሙ የቆዩ በመሆኑ ጥናት ያላጠናቀቁ ሴክተሮችም የውጤት ተኮር ምዘና ቀርቷል በሚል ከገዜ ጐፋ ፣ ዳንባ ጐፋ ፣ ዳራማሎ ፣ ቁጫ ፣ ዲታ እና ዛላ ወረዳዎች በስተቀር ምዘናው ያለመካሄዱን በተደረገው ክትትል የታየ በመሆኑ ሠራተኛው ከእቅዱ አንፃር በሜሪቱ መሠረት መመዘን ሲገባቸው በተወሰኑ ወረዳዎች እና ሴክተሮች ብቻ ማካሄዳቸው ፣ እንዲሁም የተመዘኑትንም ስንመለከት ለሠራተኛው የተሰጠው የምዝና ውጤት ከተቋሙ የአፈፃፀም ውጤት በላይ በመሆኑ በእቅድ ዝግጅቱና በምዘናው ላይ የታየው የአፈፃፀም ክፍተት እንዲተስተካከል ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀማችንን ስንመለከት 100% ለማከናወን አቅደን ይሄው 100% በዞንና በሁለም በወረዳ ተሸፍኗል፡፡

በወረዳ ደረጃ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የተከናወኑ አፈፃፀሞችን በሚመለከት ፣

ከሙከራ ተግበራ ጀምሮ ወረዳዎችን በስልጠናዎች ማብቃት የተሠራ ሲሆን የተለያዩ የማስፈፀሚያ ማኑዋሎችን በማሠራጨት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተካሂደዋል፡፡

በተጨማም የዞኑን ተሞክሮ በማሠራጨት ከመነሻ እቅድ ዝግጅት እስከ ክትትል እና ግምገማ ያሉ የማስፈፀሚያ መመሪያዎች በማድረስ እና በአካል በሥራው ቦታ በመገኘት የአቅም ማጐልበቻ ስራዎች ተከናውነው የወረዳዎች አፈፃፀም ተሻሽሏል፡፡ በዚህም በዓመቱ ወረዳዎችን 100% ለማብቃት የታቀደው ተፈፃሚ ሆኗል፡፡

- ***ጤናማና ምርታማ ዜጋ ከማፍራት አኳያ በሥርዓት ጾታና ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ሜይንስትሪሚንግ በተቋሙ በማድረግ የተመዘገቡ ውጤቶችን በሚመለከት ፣***

መምሪያችን የፈፃሚውን ግንዛቤ በማሳደግ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣ በየወሩ አንድ ቀን በሠራተኛው መካከል ውይይት በማካሄድ ፣ መልእክት አስተላለፊ ፖስተሮችን ሠራተኛው አዘውትሮ በሚገኝበት ቦታ በመለጠፍ እንዲሁም በራሪ ወረቀቶችን በማሠራጨት የሠራተኛው ግንዛቤ እንዲጐለብት የተደረገ ሲሆን ለዚሁም ሥራ ማስኬጃ እንዲሆን ከተቋሙ በጀት ላይ 2% በማስመደብ ለዚሁ አገልግሎት በማዋል አጠቃላይ የሠራተኛ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ በመፈጠሩ በተለያዩ አርዕስቶች ላይ በመወያየት እና ውሣኔዎችን በማሳለፍ ተንቀሳቅሷል፡፡ በዚህ ዓመትም በ224 ተሳታፊዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለመስራት ታቅዶ ይህ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን 6 መልዕክት አዘል ብሮሸሮች እንዲሁም ወረርሽኙን በሥራ ላይ መከላከልና መቆጣጠር መመሪያ ለ20 ዞንና ዞናዊ ባህሪይ ላላቸው መምሪያዎች ለ15ቱ ወረዳ ጽ/ቤቶች እና ለ2ቱ ከተማ አስ/አግ/ጽ/ቤቶች ተላልፎ በሥራ ላይ ውሏል ፡፡

የሴቶችን ተሣትፎ በማሳደግ የአፈፃፀም ብቃት ከማጐልበት አኳያ በተያዩ ስልጠናዎች ፣ ወርክ ሾፖች እና ስብሰባዎች እንዲሣተፋ የተደረገ ሲሆን በተቋማችን በተለያዩ ኮሚቴ አባልነት በማሳተፍ የሴቶች የአፈፃፀም አደማስ እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡

የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት በ15ቱ ወረዳዎችና በ2ቱ ከተማ አስተዳደር ከሴክተሩ በጀት ላይ 2% ከመመደብ ጀምሮ 0.05% ከሠራተኛው ደመወዝ በማዋጣት በወረርሽኙ ተጠቂ ክፍል እንዲጠቀም እያደረጉ ሲሆን የሠራተኛው ውይይትም ተጠናክሮ በመቀጠሉ የሠራተኛው አመለካከትም አድጓል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዙሪያ በ4ኛው ሩብ ዓመት ለ224 ሰው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለመስራት ታቅዶ ይሄው ተግባዊ በመሆኑ የዓመቱ ክንውን 100% ተሸፍኗል ፡፡

- ***የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ መረጃ በማሠራጨት የተከናወነ የህዝብ ግንኙነት ሥራ በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት በሚመለከት ፣***

የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ለመንግሥታዊ ተቋማት ፣ ለማህበራት እና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አፈፃፀም ፣ በመልካም አስተዳደር ፣ በፍትህ ሴክተር ቅንጅታዊ አሠራር / ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ/ ፣ በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጡ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ በዓመቱ 6 ብሮሸሮች የተሠራጩ ሲሆን ከሙከራ እስከ ሙሉ ተግበራ በአገልግሎት አሰጣጡ የታዩ ለውጦች በኤፍ.ኤም ሬዲዮ ተላልፎ ህብረተሰቡ መረጃ እንዲያገኝ ተደርጓል ፡፡

***የወረዳዎችን አፈፃፀም ስንመለከት*** በአባ ደብረ ፀሐይ ፣ በዳራማሎ ወረዳ ፣ በቁጫ ወረዳዎች ጅምር ሥራዎች የታዩ ሲሆን በሌሎች ወረዳዎች ከዞን የተላከው ከማሠራጨት ውጭ ታቅዶ የተሠራ ሥራ ባለመኖሩ ዜጐች መረጃዎችን በነፃነት

እንዲያገኙ በእቅድ የተደገፈ ሥራ መሠራት እንዳለበት ድጋፍ በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የዓመቱን ክንውን ስንመለከት በዓመቱ 6 ብሮሸሮችን ለማሠራጨት ታቅዶ ይኸው የተከናወነ በመሆኑ የዓመቱ እቅድ **100%** ተከውኗል፡፡

- ❖ **የተቋሙን ኘሮግራሞች ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ ሪፖርት ዝግጅትና አፈፃፀም ለወረዳዎችና ቀበሌያት የተደረገ ቴክኒካል ድጋፍ በሚመለከት ፣**

የወረዳዎችን አፈፃፀም በመደፍና በመከታተል ለማብቃት በእቅድ ዝግጅትና ሪፖርቲንግ ዙሪያ ከ15ቱ ወረዳ እና ከ2ቱ ከተማ አስ/አቅም ግንባታ ከተውጣጡ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ጋር ፎረም ተዘጋጅቶ ውይይት ከመደረጉም በላይ በእነዚህ ቦታ በመገኘት በእቅድ ዝግጅትና ሪፖርቲንግ ፣ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አተገባበር ፣ በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ እና በሪፎርም አፈፃፀም በአጠቃላይ በተቋሙ እቅድ አፈፃፀም ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም የወረዳዎች በእቅድ አፈፃፀም ደረጃ የተለየ ሲሆን ይህን የተሞረከዘ ድጋፍ በማድረግ የሴክተሩ አመታዊ እቅድ ሙሉ በሙሉ የሚሳካበት አቅም ተፈጥሯል ፡፡ በዚህም ዓመት 4 ጊዜ ለመደገፍ ታቅዶ ይኸው የተከናወነ በመሆኑ የዓመቱ እቅድ **100%** ተሸፍኗል፡፡

- ❖ በአንድ መ/ቤት የኔትዎርክ አፒሊኬሺን ለመዘርጋት በታቀደዉ መሠረት በመምሪያችን ሁሉም ሥራ ሂደቶች በኔት ወርክ እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀም 100%
- ❖ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ለማፍራት ለ25 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ ሴክተሮች የተወታጡ ባለሙያዎች የስልጠናዉ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይህም የዕቅዱ 100% ነዉ፡፡
- ❖ ከዞን እስከ ወረዳ ያሉትን የአይ.ሲ.ቲ መዋቅር ማደረጀትና ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶችን በማብቃት ቴክኒካል ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ በአመቱ 100 ጊዜ ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ እስአሁን 110 ጊዜ ተካሂዷል፡፡ ይህም የእቅዱ 110% ነዉ፡፡
- ❖ በአቅም ግንባታ መምሪያ ላይ ላሉ ባለሙያዎች የስካነር አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና መስጠት ከእቅዳችን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- ❖ ከፌዴራል መንግስት የተደረጉ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ስርጭቶችን 100% እንዲሳካ በማድረግ ተከናውኗል፡፡

- ❖ በወረዳዎች ላይ ለማድረግ ከታቀደው የድጋፋዊ ክትትል መርሃ-ግብር 60% በእቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡
- ❖ ከዞኑ መ/ቤቶች በቀረበልን ጥያቄ መሠረት በተለያዩ ስብሰባዎችና ስልጠናዎች ላይ የኢኮቴ (ICT) ድጋፍ በመስጠት 100% ተከናውኗል፡፡
- ❖ ከለውጥ ፕሮግራሞች የሥራ ሂደት ጋር በመተባበር ከሴክተሮች ጋር በሚደጉ ውይይቶች ላይ በመሳተፍና የአዌርነስ ሥራ 100% ተሰርቷል፡፡
- ❖ ከዞኑ ልማት ማግበር ጋር በመቀናጀት በቁጥር 75 ኮምፒውሮችን በማምጣት ለ11 ዞን መምሪያዎችና ለ2 ወረዳዎች ስርጭት ተከናውኗል፡፡
- ❖ በዞን መምሪያዎች ላይ የአይሲቲ (ICT) ባለሙያ ለመቅጠር በተደረገው ሂደት ላይ በተጠይቅን ጊዜ ፈተና በማውጣትና ውጤት በመስጠት ስራችን 100% ተከናውኗል፡፡
- ❖ በዞን መምሪያዎች ለሚገኙ ሴክረተሪያንት ታይፒስቶችና ባለሙያዎች የድጋፍና የምክር አገልግሎት 100% ተሰጥቷል፡፡
- ❖ **የተገልጋዮችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የተቋማትን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለዉ የሰዉ ሀብት ከማፍራት** ረገድ፣በጥናት ላይ የተመሰረቱ ፣ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት እጅግ ወሳኝ የሆነዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀይል በተፈለገዉ መጠን ለማፍራት አስፈላጊ የሆኑ ፣ የዕዉቀት፣ የክህሎትና ብቃት ማሳደጊያ የሚሆኑ የስራ አመራርና የለዉጥ ነክ አጫጭር ስልጠና እስከ ሀገር ዉስጥና የዉጭ አገር የረጂም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና ዕድሎችን በማስተባበር ተሠርቷል፡፡

-- በዚህ መሠረት በሀገር ዉስጥ የረዥም ጊዜ የደረጃ ማሻሻያ የትምህርት ዕድልን በተመለከተ፡-

የኢ.ሲ.ሰርቪስ ኮሌጅ ከአዋሳ ስራ አመራር ኢንስትቲዩት ጋር በተባበር በርቀት በ3 የትምህርት ዘርፎች/ በህግ፣ ማንጅሜንትና በአካዉንትንግ/ ከሰርቲፊኬት ወደ ዲፕሎማ ለማሸጋገር ለመንግስት ሠራተኞ የሚሰጠዉ የት/ዕድል ከዞናች 74 ሰራተኞ ተመልምለዉ ከተላኩ በኃላ 38 ሠራተኞች ተጣርተዉ በአርባ ምንጭ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ቱቶሪያል ማዕከል ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ክንዉን 51.65% ነዉ፡፡

- በ /ፌደራል ኤንድ ሎካል ገቨርንመንት ስቴዲስ/ በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ከዞናችን 5 ዕጩዎች ለፈተና ከቀረቡ በኃላ 1 ፈተናዉን በማለፍ በትምህርት ላይ ይገኛል፡፡ - በ4 የትምህርት ዘርፎች /አርባን ፕላንንግ ሎው ፐቢልክ ፊናንሻል ስተዲስ ዲቨሎፕምንት ኢኮኖሚክስ / 38 ዕጩዎች ለፈተና ተመልምለዉ ሁሉም ፈተና ከተቀበሉ በኃላ ዉጤታቸዉ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

- በ2002 ዓ.ም ወደ ስቪል ሰርቪስ ሎሌጅ በሁለተኛ ዲግሪ በሦስት የትምህርት ዘርፎች/ሎው ፑቪልክ ፋናንሻል ስተዲስ ዲቨሎፐምንት ኢኮኖሚክስ / ከዞናች 25 ተመልምለዉ ከተጣራ በኃላ 13 ቱ ፈተና ተቀብለዉ ዉጤታቸዉን በመጠባበቅ ላይ ይገኛ ሉ:: የዚህ ክንዉን 86.6% ይሆናል::

- ከዚህ ሌላ ለመጀመሪያ ዲግሪ በከተማ ምህንድስና በላቀ አቋም /አርባን ኢንጂነርንግ አድቫንሲድ ስታንዲንግ/ 13 ሠራተኞች፣ ያለፈተና የሚገቡ ተመልምለዉ በክልሉ አማካይነት ወደ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ተልከዋል:: ከዚህ ሌላ ለከተማ ምህንድስና 9 ከተመለመሉት 8ቱ ሚያዝያ 29 እና 30 ቀን ፈተና ተቀብለዉ ዉጤታቸዉ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ:: ክንዉን 88.1%ነዉ::

- ከዞናች ኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት አቅርቦት ከስራ ሂደት 1 ባለሙያ በፌደራል ኤሲቲ ኤጀንሲ አማካይነት ለአጭር ስልጠና ወደ ቻይና ተልከዉ በስቶረጅ ኤሪያ ኔት ዎርክ ሰልጥነዉ ተመልሷል::

- ለ 1 ባለሙያ በ/ / ፕሮግራም በግል የኒዩዝርላንድ መንግስት በሰጠዉ የ2ኛ ድግሪ የት/ዕድል ድጋፍ በመስጠት ተሸኝቷል::

❖ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ፣ የጠራ አመለካከትና የተስተካከለ አሰራርን ለማስፈን የዕዉቀት፣ የክህሎትና የብቃት ማሳደጊ ስልጠናዎች ለመስጠት የፍላጎት ስልጠና ክፍተት ጥናት ተደርጎና ታቅዶ፣ ለገጠር ወረዳ ስራ አስኪያጆችና የስራ ሂደት ሃላፊዎች አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል::

❖ የሰው ሀበት ስሚሚላት በተሰበሰበው ፍላጎት መሰረት የ5 ባለሙያዎች ቅጥር መምሪያችን ባለው ክፍት የሥራ ሂደቶች ላይ ቅጥር የተፈጸመ ሲሆን ለወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በተሰጠን ውክልና መሰረት 14 /አስራ አራት /ባለሙያዎች ቅጥር ተፈጽሚል ::
❖ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን በመቀበልና ምላሽ መስጠት በሚመለከት በአመቱ 46 ያህል አቤቱታ አቅራቢ ግለሰቦች በቅጥርና በምደባ ከተለያዩ ወረዳዎች የዞን ሴክተሮች የቀረቡ ሲሆን የእያንዳንዱ ጉዳይ ምላሽ በመስጠትና በማስተካከል ሥራ ተሰርቷል::
❖ በራስ ፈቃድ ሥራ ስሚለቁ የስንብት ደብዳቤ መስተትን በተመለከተ በግማሽ ዓመት ውስጥ ሁለት ባለሙያዎች ሥራ የመልቀቅ ጥያቄ በማቅረባቸው ለሁለቱም በጠየቁት ወቅት አፋጣኝ ምላሽ የተሰጠና በምትካቸው ባለሙያዎች ተሚልተዋል::
❖ ፈቃድ በዕቅድ መሰረት መስጠት የፈቃድ ዕቅድ በተመለከተ ከየስራ ሂደቱ የተሰበሰበ የ8 ባለሙያዎች ፈቃድ ጊዜያቸውን ያሳወቁ ቢሆንም በዕቅዳቸው መሰረት ለመውጣት ጥያቄ ያቀረቡ ባለመኖራቸው 3 ሰራተኞች ብቻ በተለያዩ ጊዜያት እንደየአጠያየቃቸው ተሰጥቷቸዋል::

***<u>ዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች</u>***

1. የታቀዱ እቅዶችና ኘሮጀክቶችን ወደተግባሪ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ወረዳዎች በእቅዱ መሠረት ተወርውሮ ድጋፍ ለመስጠት የመኪና ውስንነትና ከዚህ ጋርም ተያይዞ ያለው የቀናት ውስንነት ድጋፋዊ ክትትሉን ተደራሽ በማድረጉ ላይ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በላይ በቂ ድጋፉ እንዳይሰጥ ችግር መፍጠሩ ፣

2. በዞኑ የሚገኙ መምሪያዎች ሆነ ወረዳዎች የገቡትን ውል ከመ/ቤቱ ሠራተኞች ጋር ባለመወያየትና የጋራ ግንዛቤ ባለመጨበጥ የኘሮግራማቸው አካል ባለማድረጋቸው ለውጡ መሬት ከማውረድ አኳያ ችግር መፍጠሩ ፣

3. በየጊዜው ከሚተላለፉ መመሪያዎችና በጥናት ሰነዱ ከተቀመጠው አኳያ የሰው ኃይል አመዳደብ የተለያየ መልክ መያዘና በድጋፊዊ ክትትል ወቅት የአፈፃፀም ክፍተት መፍጠር ፣

4. ድጋፋዊ ክትትል ተደርጐ በሪፖርት ውሣኔ እንዲደረግባቸው የተቀመጡ ነጥቦች ላይ ስትሪንግ ኮሚቴው ያሳለፈው ውሣኔ ድጋፋዊ ከትትል ለሚያደርገው አለመቅረብ በቀጣዩም ለሚደረገው ድጋፋዊ ክትትል ተጽዕኖ ማሳደሩ ፣

5. የክልል የሥራ ሂደት የዞኑን ባለሙያች ለመደገፍና ለማብቃት እየተደረገ ያለው አፈፃፀም ደካማ ከመሆኑም ባሻገር የሥራ ሂደቱ ሌሎችን ተቋማት የማብቃት ሥራ የሚሠራ ሆኖ እያለ የተለያዩ ሥልጠናዎች ሲሰጡ የዚህ ሥራ ሂደት አባላት እንዲሣተፉ ባለመደረጉ ለአዳዲስ መረጃዎች እና አሠራሮች እንዳግዳ መሆንን ፈጥሯል ፣
6. ሂደቱ የማያከናውነው በአብዛኛው የአቅም ግንባታ ሥራዎች ስብሰባ ፣ ፎረም ፣ ምክክር ጉባኤ በአጫጭር ስልጠናዎች አቅም የሚፈጠር ሲሆን ይህን ለመፈፀም የመሰብሰቢያ አዳራሽ የሌለውና በሌላ ሴክተር እጅ የሚገኙትም በተለያዩ ኘሮግራሞች ስለሚያዙ የኘሮግራሞች መፋለስ እና የእቅድ መውደቅ ማጋጠሙ ፣

7. የለውጡም ሆነ የሪፎርሙ ሥራ የኃላፊዎች ተቀዳሚ ኘሮጀክት እንደሆነ የተቀመጠ ቢሆንም ከተወሰኑ ኃላፊዎች በስተቀር ለድጋፍና ትብብር ያላቸው ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን ፣

## ***የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

1. መምሪያው ለውጡን የመምራትና የማስፈፀም ከፍተኛ ኃፊነት ያለበት በመሆኑ ያገኘ ውን አጋጣሚ እና የመጨረሻ አማራጮችን በመጠቀም በትራንስፖርትና በዞን በሚገኘ - መምሪያዎች እና ገጠር ቀበሌያት በእግር በመንቀሳቀስ እቅዱ እንዲሣካ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

2. እየተፈጠረ ያለውን  የጊዜ መጣረዝ ለማካካስ እቅዶችን አጣምሮ በመውረድና የወረዳ አስፈፃሚና እና ፈፃሚ አካላትን ወደአንድ ማዕከል በማሰባሰብ እቅዱ እንዲሳካ ጥረት ተደርጓል፡፡

3. የሚነሱ ተግዳሮቶችን በመቀነስ ሠራተኛውን ወደ ለውጡ ለማስገባት የየሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የጋራ ወርሃዊ የውይይት መድረክ  ተዘጋጅቶ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ውይይት እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡

4. ያለውን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ችግር ለመቋቋም የመሰብሰቢያ ቀናት በማዘዋወር ፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆነ ክፍሎችን በማፈላለግ እና ወንበሮች ከየቦታው በማሰባሰብ የእለቱ አጀንዳ እና ሰብሰበሳ እንዳይፋለስ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ፡፡

5. በተመሳሳይ መልኩ ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው ሴክተሮች ከድጋፋዊ ክትትል ባሻገር በ15 ቀን አንድ ቀን የሠራተኛ በወር አንድ ቀን የሪፎርም አካላት የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

# <u>የዞን አ/ግንባታ መምሪያ  የ2001 ዓ.ም ዓመታዊ  የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማጠናቀሪያ</u>

## <u>ቅጽ፤</u>

## <u>*የዕቅድ ዘመን 2001 ዓም*</u>

| ተ.ቁ | ግቦችና ዝርዝር ተግባራት | መለኪ. ያ | ዕቅድ | | | ክንውን | | ክንውን % እስከዚህ ሩብ ዓመት ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር | | | ሥራው የተከናወነበት ቦታ | ፈጻሚ አካል | ምርመ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የዓመቱ | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚ. ህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመ ት | እስከዚ. ህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት ክንውን | የእስከዚህ ሩብ ዓመት | የእስከዚህ ሩብ ዓመት ክንውን ከዓመታዊ ዕቅድ | | | |
| 1 | የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ባጠናቀቁ 7 ሴክተሮች ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ለማሸጋገር የተደረገ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል | በዙር | 3 ዙር | 1 | 3 | 1 | 3 | 33.3% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/ የፕ/ጥ/ት | |
| 2 | የኢንስፔክሽን አደረጃጀት ስርዓት ለመዘርጋት የተደረገ ሙዊ ድጋፍና ክትትል | በዙር | 4 ዙር | 1 | 4 | 1 | 4 | 25% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |
| 3 | ኅብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሣተፍና አሣምኖ ማሠራትን ባህል ለማዳበር ግልፅና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራርና ሞዴል የመጠቀም የተዘረጋ ስርዓት፣ | በዙር | 4 ዙር | 1 | 4 | 1 | 4 | 25% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በዞኑ  የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ዉጤታማ ለማድረግ የተዘጋጀው ፎረም የፈጠረው ግንዛቤ | በዙር | 3 ዙር | 1 | 3 | 1 | 3 | 33.3% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |
| 5 | የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት ሥርዓት ለመዘረጋት የተደረገ ድገሰፋዊ ክትትል | በዙር | 4 ዙር | 1 | 4 | 1 | 4 | 25% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |
| 6 | የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲን በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በማስረጽ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣናና ዉጤታማ እንዲሆን የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል | በዙር | 3 ዙር | 1 | 3 | 1 | 3 | 33.3% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |
| 7 | ከዞን እስከ ወረዳ በስቴራቴጂክ ዕቅድ አመራር በዓመታዊ ዕቅድና ዉጤት ተኮር ዕቅድ አሠራር ሥርዓተ በማስተላለፍ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት እንደ ሥርዓት መትከል፣ | በዙር | 3 ዙር | 1 | 3 | 1 | 3 | 33.3% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |
| 8 | የተጠናከረ የሥርዓተ ጾታና ፀረ ኤች አይቭ / ኤዲስ / ሚይንስትሪሚንግ ሥርዓት መዘርጋት | በቁጥ ር | 224 | 112 | 224 | 112 | 224 | 50% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፕ/የ ፕ/ጥ/ት | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ለ 15 ወረዳዎች የተደረገ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ድጋፍ | በዙር | 3 ዙር | 1 | 3 | 1 | 3 | 33.3% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፐ/የ ፐ/ጥ/ት | |
| 10 | ለህ/ተሰቡ በብሮሽር የተሰራጨ መረጃ | በቁጥ ር | 6 | 1 | 6 | 1 | 6 | 16.7% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የለ/ፐ/የ ፐ/ጥ/ት | |
| 11 | በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች በዕቅድ ሪፖርት ዝግጅትና አፈፃፀም ለወረዳና ቀበሌ የተደረገ ድጋፍ፣ | በዙር | 4 ዙር | 1 | 4 | 1 | 4 | 25% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባ | የለ/ፐ/የ ፐ/ጥ/ት | |
| 12 | የሰው ሀብት ፍላጎት ዕቅድ ማዘጋጀት | በቁጥ ር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 100% | 100% | አቅም ግንባታ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |
| 13 | የሰው ሀብት ማሟላት | በቁጥ ር | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 100% | 100% | 100% | ዞን አ ቅም ግንባ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |
| 14 | አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን መቀበልና ምላሽ መሰረጠት | በቁጥ ር | እንደየአ መጣጡ | እንደየ አመ ጣጡ | እንደየ አመ ጣጡ | 44 | 44 | 100% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |
| 15 | በራስ ፈቃድ ሥራ ለሚለቁ የስንብት ደብዳቤ መስጠት | በቁጥ ር | እንደየአ መጣጡ | እንደየ አመ ጣ | እንደየ አ | 2 | 2 | 100% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የፈቃድ በዕቅድ መሰረት መስጠት | በጊዜ | 8 | 8 | 8 | 3 | 3 | 100% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |
| 17 | የትብብርና ድጋፍ ደብዳቤ መስጠት | በቁጥር | እንደየአመጣጡ | እንደየአመጣጡ | እንደየአመጣ | 24 | 24 | 100% | 100% | 100% | ዞን አቅም ግንባታ | የሰው ሀብት ሥራ አመራር | |
| 18 | ከዞን እስከ ወረዳ ያሉትን የ ICT / መዋቅር ማደራጀትና ለሌሎች ሴክተር መሥ/ቤቶችን ለማብቃት የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ፣ | በቁጥር | 100 | 25 | 100 | 30 | 110 | 30% | 110% | 110% | ዞን አቅም ግንባታ | የኢኮቴ መ/ልማት | |
| 19 | የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ለማፍራት ለ25 ሰዎች የተሰጠ ስልጠና | በዙር | 4 | 1 | 4 | 1 | 1 | 25% | 25% | 25% | ዞን አቅም ግንባታ | የኢኮቴ መ/ልማት | |
| 20 | የአሰራር ሥርዓተ ጥናት /BPR/ ለተገበሩ የሥራ ሂደቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ / automate the busuness process | በዙር | 60 | 60 | 60 | 60 | 60 | 100% | 100% | 100% | በዞን መምሪያዎች | የኢኮቴ መ/ልማት | |
| 21 | የኔት ዎርክ አፒሊኬሺን ለአንድ መ/ቤት መዘርጋት | በዙር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን መምሪያዎች | የኢኮቴ መ/ልማት | |
| 22 | በዞኑ ካሉ ሴክተሮች ጋር በሚደረገው የውይይት መድረክ ላይ የአዌርነስ ሥራ መስራት | በዙር | 4 | 1 | 4 | 1 | 4 | 25% | 100% | 100% | በዞን ፖሊስ አዳራሽ | የኢኮቴ መ/ልማት | |
| 23 | ለአቅም ግንባታ ሴክተር ባለሙያዎች የስካነር አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት | በዙር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን አ/ ግንባታ | የኢኮቴ መ/ልማት | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **24** | ለመምሪያው የሚያስፈልጉ ወቅታዊ መረጃዎችን መሰብሰብና አጠናቅሮ ማቅረብ | በቁጥር | **8** | **4** | **8** | **3** | **7** | **37.5%** | **37.5 %** | **87.5%** | በዞን አ/ግንባታ | የመረጃ መ/ማ የሥራ ሂደት | |
| **25** | የተጣሩትን መረጃዎች ዓይነት በየአስተዳደር እርከኑ በተገልጋች ፍላጎት መሰረት በማደራጀት የተደራጀውን መረጃ ለዞን ዋና የሥራ ሂደት ማስተላለፍ | በዙር | **2** | **1** | **2** | **1** | **2** | **50%** | **100%** | **100%** | በዞን አ/ግንባታ | የመረጃ መ/ማ የሥራ ሂደት | ስታንዳርድ ፎርማት ባለመድረሱ |
| **26** | በወረዳዎችና በ2ቱ ከተማ አስተዳደሮች ለመስክ ግምገማ ቢጋር ማዘጋጀት | በዙር | **2** | **1** | **2** | **1** | **1** | **50%** | **50%** | **50%** | በዞን አ/ግንባታ | የመረጃ መ/ማ የሥራ ሂደት | በተሸከርካሪና በሌሎች ምክንያቶች የ2ኛው ዙር ድጋፋዊ ክትትል አልተደረገም |
| **27** | የሥራ ሂደቱን በሚመለከቱ ልዩ ልዩ ወርክ ሾፖችና አውደጥናቶች ስልጠናዎች ላይ በሳተፍ | በቁጥር | እንደየአመጣጡ | **3** | **3** | **3** | **3** | **100%** | **100%** | **100%** | አዋሳ ሥራ አመራር | የመረጃ መ/ማ የሥራ ሂደት | |
| **28** | በ2001 ዓም ወደ ሲቪል ሰርቪስ የሚገቡ ዕጩዎች ምዝገባ | | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | |
| | • በመጀመሪያ ድግሪ | በቁጥር | 74 | - | 38 | - | 38 | - | 51.65 % | 51፣65% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| | • በ2ኛ ድግሪ | በቁጥር | 5 | 2 | 5 | 1 | 1 | 20% | 20% | 20% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| | • በሪቀት ትምህርት ለመጀመሪያ ድግሪ | በቁጥር | 74 | - | 38 | - | 38 | - | 51.65 % | 51.65% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| | • የተሰጠ የውጪ ሀገር የት/ዕድል በ2ኛ ድግሪ | በቁጥር | 2 | - | 2 | - | 1 | - | 50% | 50% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሓብት ልማት | |
| | • ለ2ኛ ድግሪ ተመለመሉ ሴቶች | በቁጥር | 2 | - | 2 | - | 1 | - | 50% | 50% | በዞን አ/ግን | የሰው ሀብት ልማት | |
| 29 | 1 የተቀረጸ የስልጠና ፈንድ ማፈላለጊያ ፕሮጀክት | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| 30 | የተዘጋጀ የስልጠና መገምገሚያ ቅጽ | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| 31 | የተዘጋጀ የብቁ የተገልጋዮች መብትና ግዴታ ማሳወቂያ ጽሁፍ | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| 32 | የተደረገ የስልጠና ግምገማ | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 33 | በሙሉ ትግበራ ድልድል ወቅት ለወረዳ ሰክተር ጽ/ቤቶች የተሰጠ ድጋፍ | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በወረዳዎች | የሰው ሀብት ልማት | |
| 34 | ለወረዳዎች የተላከ የት/ት እና ስልጠና ምልመላ መመሪያ | በቁጥር | 1 | - | 1 | - | 1 | - | 100% | 100% | በወረዳዎች | የሰው ሀብት ልማት | |
| 35 | ለወረዳ አ/ግንባታ የሰው ሀብት ልማት የሥራ ሂደት ፈጻሚዎች የተሰጠ ስልጠና | በቁጥር | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 50% | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | የሰው ሀብት ልማት | |
| 37 | በአ/ግንባታ መምሪያ ውስጥ ያሉ የስራ ሂደቶች ዕቅድ ክለሳ ወቅት ድጋፋዊ ክትትል ማድረግና ዕቅዶችን ማደራጀት | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 100% | 100% | በዞን አ/ግንባታ | በልማት ዕ/ዝ/ክ/የሥራ ሂደት | |
| 38 | በሴክተሩ የወረዳዎች ዓመታዊ የልማት ዕቅድ የየሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት መቀበል ማጠቃለልና ግብረመልስ መስጠት | በቁጥር | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 100% | 50% | በዞን አ/ግንባታ | በልማት ዕ/ዝ/ክ/የሥራ ሂደት | |